የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ
የፌደሬሽን ምክር ቤት

The House of Federation
of
The Federal Democratic Republic
of Ethiopia

ቁጥር ፌዴ/ም/ፌ/ሕ/ዳ/26/5/309
No
ቀን 23/02/2011
Date

ለወ/ሮ ኤልሳቤጥ አበበ ተወካይ ሻምበል ልሳነወርቅ በትሩ

ባሉበት

ጉዳዩ፡- የምክር ቤቱን ውሳኔ ስለማሳወቅ

እርስዎ የሕገ-መንግስት ትርጉም አቤቱታ ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ማቅረብዎ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የፌዴሬሽን ምክር ቤት መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም በ5ኛ የፓርላማ ዘመን 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ ባቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ላይ ከፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው አይደለም በማለት የሰጠውን የውሳኔ ግልባጭ 5/አምስት/ ገጽ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ ሰጥተንዎታል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ከሪያ ኢብራሂም አቢ
የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ-ጉባኤ

ግልባጭ

- ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

አዲስ አበባ

- ለሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

በፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን

4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ ኤልሳቤጥ አበበ ተወካይ ሻምበል ልሳነወርቅ በትሩ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. የጅግጅጋ ከተማ የ01 ቀበሌ አስተዳደር

2ኛ. እነ አቶ ደስታ ካሳ (5 ሰዎች)

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ የከተማ ቤት ባለቤትነት መብት በፍርድ ከተረጋገጠ በኂላ በአፈጻጸም ለመረከብ የቀረበ ክርክር የሚመለከት ሲሆን፣ አመልካች በጅግጅጋ ከተማ 01 ቀበሌ በ600 ካ.ሜ ላይ የተሰሩ 5 ክፍል ቤቶች በባለቤቴ ሟች ሻለቃ ሞገስ ገ/ማሪያም ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ያልተወረሰ ቤት ለምስራቅ ቀጠና በአደራ በመስጠት በለውጡ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 21 ቀበሌ 19 የቤት ቁጥር 435 የሆነውን የኪራይ ልዩነት በመክፈል ስንኖር አዲስ አበባ በለውጥ የተያዘው ቤት ኪራዩ በመጨመሩ የጅግጅጋውን ቤት ከኪራይ ቤቶች የተረከበው የሶማሌ ክልላዊ መንግስት እንዲያስረክበን በተለያዩ አካላት በጽሁፍ ሲገለጽ 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ውስጥ ያሉ ሌሎች ተጠሪዎች በማስለቀቅ ሊያስረክበን ፈቃደኛ ስላልሆነ በፍርድ ተገደው እንዲያስረክቡ እንዲወሰን ሲሉ ለሱማሌ ክልል ጂግጂጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወሰዱ ቤቶችን የሚመለከት ክስ የማየት ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሰረት የፍ/ቤት ሳይሆን የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነው፣ የአመልካች ልጅ አካለ መጠን ስላልደረሰ ክስ ለማቅረብ ስልጣን የላቸውም እና ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው የሚሉ የተለያዩ ሶስት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ብቻ በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

የጅግጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ለአመልካች ቤቶቹን እንዲያስረክቡ ሲል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች ለሱማሌ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ የተሰጠው ውሳኔ ግድፈት የሌለበት ነው በማለት የበታች ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 20/07/07 ዓ.ም በተጻፈ ያቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ በሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው የተመረመረ ሲሆን አመልካች የፍርድ ባለመብት መሆናቸውን ካቀረቧቸው ውሳኔዎች ቢረጋገጥም እንደ ፍርዱ እንዲፈጸምላቸው ስለመጠየቃቸው የቀረበ አስረጂ ስለሌለ ይህን እንዲያሟሉ ሲጠየቁ፤ በጅግጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በቁጥር 784/97 በቀን 18/06/03 ዓ.ም የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት ተጠሪዎች በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ቤቱን እንዲያስረክቡ የተሰጠ ትዕዛዝ፣ በሶማሌ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በቁጥር 05-1-238/01 በቀን 02/12/03 እና በቁጥር 14/409/04 በቀን 16/01/04 ዓ.ም በተጻፈ የከፍተኛ ፍ/ቤቱን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በመጥቀስ እንደፍርዱ እንዲያስፈጽሙ ለጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር እና ለጅግጅጋ ከተማ ፀጥታ ዘርፍ ጽ/ቤት የተሰጡ ትዕዛዞችን አቅርበዋል፡፡

በተጨማሪም ከላይ ለተሰጠ የአፈጻጸም ትዕዛዝ መነሻ የሆኑት ፍርዶች በሌሎች የበላይ ፍ/ቤቶች እንዳልተሻሩ እና እንደፍርዱ መፈፀም ያልተቻለበትን ሁኔታ ለማወቅ በተደረገ ማጣራት የጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር እና የቀበሌ 01 አስተዳደር በጋራ በጉዳዩ ላይ በመነጋገር በጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት አድራሻ በቁጥር MMI1/560/09 በቀን 03/08/09 ዓ.ም በተጻፈ ምላሽ እንደፍርዱ እንዲፈፀም የአፈጻጸም መጥሪያ ወይም ትዕዛዝ ለፍርድ ባለዕዳው ባለመድረሱ እና ስላፈጻጸሙ ምላሽ ያልሰጡ በመሆኑ ውሳኔው ሊፈፀም እንዳልቻለ ተገልጿል፡፡

በሌላ በኩል በተመሳሳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የጅግጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ለቀረበላቸው ጥያቄ በጉዳዩ ላይ በጋራ በመነጋገር በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አድራሻ በቁጥር M-G/453/09 በቀን 18/08/09 ዓ.ም በተጻፈ ምላሽ ውሳኔው እስከ አሁን ሊፈፀም ያልቻለው ቤቶቹ የመንግስት ናቸው አይደሉም የሚል ግጭትና ችግር ያስነሳ የነበረ በመሆኑ፣ አመልካች ለብዙ ዓመታት ጉዳዩን ሳይከታተሉ እና አቤቱታ አቅርበው መዝገብ እንዲንቀሳቀስ ባለማድረጋቸው እንደሆነ ገልጾ፤ እንደውሳኔው እንዲፈፀም የአፈጻጸም መዝገብ በማንቀሳቀስ እንዲረከቡ እና በቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ግለሰቦች ተለዋጭ ቤት እንዲፈለግላቸው ማድረግ መፍትሄ ሆኖ እንዳገኘው አሳውቋል፡፡

ጉባዔውም ባደረገው ምርመራ አመልካች በጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ በ600 ካ.ሜ ስፍራ ተገንብተው ለሚገኙ ቤቶች ባለቤት መሆናቸውን ፍ/ቤቶች ለውሳኔያቸው መሰረት ካደረጓቸው ተገቢ ስረጃዎች እና በህግ አግባብ በተደረገ ክርክር ከተሰጠ ፍርድ ላይ ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፤ ይህ የፍርድ ባለመብትነት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከመጽናቱ በቀር እንዳልተሻረ በዋናነት ከፍርድ ባለዕዳው እና ከፍርድ አስፈጻሚ ፍ/ቤቶች ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስለዚህ አመልካች በአቤቱታቸው ተጥሷል የሚሉትን ህገ መንግስታዊ መብት ያመላከቱ ባይሆንም በፍርድ ለተጠቀሰው ቤት በጉልበታቸው የተፈራ የግል ንብረት ባለቤትነታቸው ተረጋግጦ እንዲረከቡ ተወስኖ እያለ፤ በዚህ የግል ንብረታቸው ላይ ያላቸውን የመያዝ፣ የመጠቀም ወይም የማስተላለፍ የንብረት መብት ከውሳኔ ባሻገር በፍርድ አፈጻጸም በሚደረግ ማስረከብ የግል ንብረት ባለቤትነት መብትን የማስከበሪያ መንገድ መሆኑ እየታወቀ ለረጅም ዓመታት የተደረገው የአፈጻጸም መዘግየት ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 የግል ንብረት መብት የሚቃረን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

እንዲሁም ፍ/ቤቶች በፍርድ የወሰኑትን መብት ማስፈፀም የሚቻለው በተመሳሳይ ለወሰነው ፍ/ቤት ለአፈጻጸም ዳኝነት በማቅረብ እንደሆነ የፍትህ ብሔር ስነ ስርዓት ህጉ በግልጽ ደንግጎ ስለሚገኝ በአመልካች የቀረበላቸውን የአፈጻጸም ጥያቄ በተለያዩ ትእዛዛት፣ ውሳኔ ወይም ፍርድ እንደፍርዱ ማስፈፀም ሲገባቸው ይህን አለማድረጋቸው ከኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 ንኡስ አንቀጽ 1 ፍትህ የማግኘት መብት የሚቃረን ተግባር መፈጸማቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች እንደፍርዱ እንዲፈጸምላቸው ላቀረቡት የፍርድ መብት የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት ተጠሪዎች የማይፈጽሙበት ምክንያት ካለ ቀርበው እንዲያስረዱ በማድረግ በገለልተኛነት ክርክሩን በመመርመር መወሰን ሲገባቸው፤ የአፈጻጸም መጥሪያ ወይም ትዕዛዝ የፍርድ ባለዕዳ ለሆኑት ተጠሪዎች ደርሶ ምላሽ እንዲሰጡ ባልተደረገበት ሁኔታ የተጀመረውን የፍርድ ማስፈጸም ተግባር በራስ ተነሳሽነት በማቋረጥ እና በጉባዔው ጥያቄ መሰረት ውሳኔው እስከ አሁን ማስፈጸም ያልቻለው ቤቶች የመንግስት ናቸው አይደሉም የሚል ግጭትና ችግር ያስነሳ የነበረ በመሆኑ፣ አመልካች ለብዙ ዓመታት ጉዳዩን ሳይከታተሉ እና አቤቱታ አቅርበው መዝገብ እንዲንቀሳቀስ ባለማድረጋቸው እንደሆነ ገልጸው፤ እንደውሳኔው እንዲፈፀም የአፈጻጸም መዝገብ በማንቀሳቀስ እንዲረከቡ እና በቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ግለሰቦች ተለዋጭ ቤት እንዲፈለግላቸው ማድረግ መፍትሄ ሆኖ እንደተገኘ የተሠጡ ምላሾች ከፍርድ ባለዕዳው ምላሽ ጋር የሚቃረን ነው፡፡

በሌላ በኩል በፍርድ ባለዕዳው ያልተነሳ መከራከሪያን ፍ/ቤቱ በማንሳት እንደፍርዱ ላለማስፈጸም ያሳየው ፈቃደኝነት ማጣት ከኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 79 ንኡስ አንቀጽ 3 ፍ/ቤቶችና ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ያከናውናሉ፡፡ ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም ከሚለው የዳኝነት ስልጣን በሚርቅ ሁኔታ ለተጠሪ በግልጽ በማድላት፣ በመወገን እና በህግ

ከተቀመጠው የክርክር አመራር በመውጣት የሄደበት አግባብ ነጻ እንዳልሆነ እና በህግ እንዳልተመራ የሚያረጋግጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለዚህ በጉዳዩ ላይ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 ፍትህ የማግኘት እና 40 ንዑስ አንቀጽ 4 የንብረት መብቶች እንዲሁም ከዳኝነት ስልጣን ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ ጋር የሚጋጭ ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሀሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ በሕገመንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴው ጉዳዩ ታይቶ እንዲቀርብ መርቶት ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኂላ አመልካች በጅግጅጋ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ በስድስት መቶ ካ.ሜ. ላይ የተሰሩ አምስት ክፍል ቤቶች በባለቤታቸው ሚች ሻለቃ ሞገስ ገ/ማርያም ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ሆኖ በ1972 አ.ም በስራ ምክንያት ሲዛወሩ ቤቱ ለምስራቅ ቀጠና በአደራ ተሰጥቶ በብር 70 (ሰባ ብር ) ተከራይቶ በለውጥ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 21 ቀበሌ 19 የሚገኘው የቤት ቁጥር 435 ኪራዩ 160 ብር የሆነ ቤት ውስጥ የኪራይ ልዩነቱን በመክፈል ሲኖሩ ከቆዩ በኂላ የአዲስ አበባው ቤት ኪራዩ በመጨመሩ የጂግጂጋው ቤት እንዲመለስላቸው ለሚመለከታቸው አካላት ጥያቄ አቅርበው እንዲመለስላቸው የተወሰነ በመሆኑ የአሁን ተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ሲጠይቁ ቤቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ለሶማሌ ክልል የጂግጂጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ክስ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን አጣርቶ ቤቱ ለአሁን አመልካች እንዲመለስ መወሰኑን፣ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ማጽናቱን፣ የአሁን አመልካች ቤቱን በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት ለመረከብ የፍርድ አፈጻጸም ክስ አቅርበው የጂግጂጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁ. 784/97 በ18/06/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፍርድ ባለእዳው የጂግጂጋ ከተማ ቀበሌ 01 አስተዳደር ጽህፈት ቤት ክርክር የተነሳበት ቤት ውስጥ እየኖሩ ያሉ ግለሰቦችን በማስለቀቅ ቤቱን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለፍርድ ባለመብት እንዲያስረክብ ትእዛዝ ቢሰጥም በትእዛዙ መሰረት እንደ ፍርዱ ያልተፈጸመ መሆኑን ምክር ቤቱ ተረድቷል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 386 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ፍርድ የሚፈጸምበትን የአሰራር ስነ ስርአት ተከትሎ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት ማስፈጸም ሲገባው ይህን አለማድረጉን ከቀረበው መዝገብ መረዳት የተቻለ ሲሆን ክርክር የተነሳበት

ቤት ለአሁን አመልካች ሊመለስ እንደሚገባ ውሳኔ ያገኘና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም የጸና ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ስልጣኑን ተጠቅሞ የፍርድ ባለእዳዎች ተገደው እንደ ፍርዱ እንዲፈጽሙ ማድረግ ሲገባው ይህን አለማድረጉ በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ኂላፊነት በሚገባ አለመወጣቱን ያሳያል፡፡

ይሁንና አሁን የተያዘው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ እልባት ማግኘት የሚገባው ጉዳዩን በያዙት እና የሰጡትን ፍርድ የማስፈፀም ስልጣን በተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች እንጂ ሕገ መንግስቱን በሚተረጉመው የፌዴሬሽን ምክር ቤት አይደለም፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ስልጣን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ሕገ መንግስቱን የሚቃረን ውሳኔ ሲሰጥ የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት የዜጎችን ሕገ መንግስታዊ መብት ማስከበር እንጂ ፍርድ ቤቶች ሕገ መንግስቱን የሚቃረን ውሳኔ ባልሰጡበት ሁኔታ በፍርድ ቤቶች ስራ በመግባት የፍርድ አፈጻጸም ስራ የሚሰራበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ አመልካች የከፈቱትን የፍርድ አፈጻጸም ክስ ተከታትለው በውሳኔው መሰረት የማይፈጸምላቸው ከሆነ ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የአፈጻጸም ትእዛዝ ላይ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ በይግባኝና በሰበር ማሳረም የሚችሉበት የሕግ ስርአት ተዘባለበት ሁኔታ ፍትህ የማግኘት መብት ተጥሷል የሚያስብል ነገር የለውም፡፡ ምክንያቱም አመልካች ጉዳያቸው በፍርድ ቤቶች ሲታይ ቆይቶ ፍርድ ቤቶችም ሕጉን መሰረት ያደረገ ውሳኔ በመስጠታቸው ምክንያት አመልካች የፍርድ ባለመብት መሆናቸው ሲታይ ፍትህ የማግኘት መብታቸው መጣሱን አያመለክትም፡፡ ፍርድ የማስፈፀም ጉዳዩም በተመሳሳይ የሕግ ስርዓት በፍርድ ቤቶች የሚያልቅ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም ከፍ ብሎ በተጠቀሱት ምክንያቶች የአሁን አመልካች አቤቱታ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ከሕገ መንግስት ትርጉም መርህ እና አላማ ጋር የሚጣጣም ሆኖ ስላልተገኘ ምክር ቤቱ የረበውን የውሳኔ ሀሳብ ባለመቀበል ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ወስኗል፡፡

## ትእዛዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለባለጉዳዩ ይሰጥ፡፡
2. የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያውቀው ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይላክ፡፡